ብፁዕ ወቅዱስ ዶ/ር አቡነ ጳውሎስ ቀዳማዊ ፓትርያርክ፣ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳሳ ዘአክሱም፣ ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ፕሬዚዳንት ለ ሐመር መጽሔት ዝግጅት ክፍል በ1991 ዓ.ም ስለ



- *ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ አገልግሎት*
- *ንዋያተ ቅዱሳት አጠባበቅ*
- *ዘመናዊ የቤተ ክርስቲያን የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት*
- *ገጠሪቱ ቤተክርስቲያ (አብነት ት/ቤቶችና ገዳማት )*
- *ቤተክርስቲያን ለጥቁር አፍሪካውያን ለመድረስ ያላትን ዝግጁነትና አለማቅፋዊ አገልግሎት*
- *የወጣቶች አገልግሎትና የሰንበት ት/ቤት መርሐግብር*
- *የግል ሕይወታቸውና ሌሎች ጉዳዮች ላይ የሰጡትን ቃለ ምልልስ እንደሚከተለው አስተናግደነዋል።*

## **"የኢትዮጵያ መምህሯ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ነው፡፡"**

*ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፖትርያርክ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት ጥቅምት 25 ቀን 1928 በትግራይ አድዋ አውራጃ እንዳ አባ ገሪማ በተባለው ቦታ ከአፈ መምህር ገብረ ዮሐንስ ወልደ ሥላሴና ከወ/ሮ አርአዶች ተድላ ተወለዱ፡፡*

*ቅዱስነታቸው ከልጅነታቸው ጀምሮ በአንዳ አባ ገሪማ፣ በጭኸና በአባ ሐደራ ገዳማት የቤተ ክርስቲያን ትምህርት፤ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንንና የአበው መነኮሳት ሥርዓትን የተከተለ ገዳማዊ ኑሮን እያጠኑና አባቶቻቸውን እያገለገሉ ካደጉ በኋላ በአባ ገሪማ ገዳም ሥርዓተ ምንኩስናን ተቀበሉ፡፡ ቀደም ሲልም ዲቁናን ከአቡነ ማርቆስ ቅስናን ከአቡነ ይስሐቅ ከተቀበሉ በኋላ ገዳማዊ አገልግሎታቸውን በመቀጠል ኢያሴ ትሩፋትን ፈጽመዋል፡፡*

*ከዚህ በኋላ በ1949 ዓ.ም. ወደ አዲስ አበባ መጥተው በመንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል የአንደኛና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ከመንፈሳዊ ትምህርትና አገልግሎት ጋር አጠናቀቁ፡፡ ወደውጭ አገር በመጓዝም ለ16 ዓመታት በተለዩዩ ዩኒቨርስቲዎች በመዘዋወር በአሜሪካ ከቅዱስ ቭላድሚር የራሺያ ኦርቶዶክስ መንፈሳዊ ኮሌጅ ዲፕሎማ ኦፍ ግራጁዌትና በኦርየንታልና በምሥራቅ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት መካከል ባለው የነገረ መለኮት ትምህርት ዲፕሎማ፣ ከየል ዩኒቨርስቲ በኦርየንትል በምሥራቅና በምዕራባውያን አብያተ ክርስቲያናት መካከል ባለው የነገረ መለኮት አመለካከትና ልዩነት ባችለር ኦፍ ዲቪኒቲ /B.D/፣ ከፕሪስተን ዩኒቨርስቲ በክርስቲያን ሥነ ምግባር /Christain Ethics/ የማስትሬት ዲግሪና በከፍተኛ የነገረ መለኮት ትምህርት ዶክትሬት /PH.D/ ተቀብለው ወደ አገራቸው ተመለሱ፡፡*

*ወደ አገራቸው ከተመለሱ በኋላ የድርስትና የስብከት እንዲሁም የእሑድ ትምህርት ቤት የበላይ ሓላፊ፣ የሰዋሰው ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ መንፈሳዊ ትምህርት ቤት ዲን፣ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር የስደተኞች ጽ/ቤት ዋና ጸሓፊ፣ ቆይቶም የኮሚሽኑ ተቀዳሚ ሥራ አስኪያጅ በመሆን አገልግለዋል፡፡*

*ቅዱስነታቸው መስከረም 16 /1968 ዓ.ም. ጵጵስናን ከብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ የተቀበሉ ሲሆን በቀድሞው የደርግ መንግሥት ለሰባት ዓመታት ያህል ለእሥር ተዳርገው ነበር፡፡ ከእሥር ከተፈቱም በኋላም ለ8 ዓመታት በአሜሪካን አገር ቤተ ክርስቲያንን አገልግለዋል፡፡*

*ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ሰኔ 28/1984 ዓ.ም. አምስተኛው የኢትዮጵያ ፓትርያርክ በመሆን ተመርጠዋል፡፡*

ቅዱስነታቸውን በልዩ ልዩ የቤተ ክርስቲያን ጉዳዮች ዙሪያ አነጋግረናቸዋል፡፡

*ሐመር*፡- ከብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ጋር ብዙ ዘመናትን እንዳሳለፉ ይታወቃል፡፡ እስቲ ስለ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ጥቂት ይንገሩን?

*ቅዱስነታቸው*፡- በእውነቱ ልጆቼ እኒህ አባት ማን ናቸው? እስቲ ስለ እርሳቸው ንገረን ብላችሁ ስለጠየቃችሁኝ እጅግ ደስ ብሎኛል፡፡ ምክንያቱም ምንም እንኳ ለጥቂት ጊዜያት ቢሆንም ከእኒህ ቅዱስ አባት ጋር ቆይቼ ማንነታቸውን በሚገባ ተረድቼዋለሁና፡፡

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ በኢትዮጵያ ውስጥ ከነበሩት ከታላላቅ ምሁራን አንዱ ምናልባትም የበለጡ ነበሩ፡፡ ቅዱስነታቸው የበላይነት ስሜት ያልነበራቸው፣ የሚያውቁትን እኔ ልናገር የማይሉ፣ ሁሉንም በትዕግሥት የሚያዳምጡ፣ ከሁሉም ጋር በትዕግሥት የሚኖሩ አባት ነበሩ፡፡ ምናልባት ሰው ዝምተኛነታቸውን በኩራት፣ ትዕግሥተኛነትቸውን በስንፍና እኔ አለሁ ሊቅ ብለው አለመፎከራቸውን እንዲሁ እንዳልተማሩ አድርጎ ሊወስድባቸው ይችላል፡፡ መቼም ዓለሙ አስቸጋሪ ነውና፡፡

ቅዱስነታቸው ብዙ ጊዜ በተለይ ለመማር ፍላጎት ያለውን ሰው ያጠኑ ነበር፡፡ ይህ ጠባያቸው አዲስ አበባ ለሚመጣላቸው ሰው ብቻ አልነበረም፡፡ የትም ቦታ ሔደው እንደዚያ ዓይነት ሰው ካዩ እንዲማር ሁኔታዎችን ያመቻቹለት ነበር፡፡

ሌላው አንድ ሰው መጥቶ አንድ ነገር ያመለክታል፡፡ ይሰሙትና የሚሆነውን ነግረው ይሰዱታል፡፡ ውሎ አድሮ ደግሞ ያው ሰው መጥቶ ያንኑ ነገር ሊያስረዳቸው ሁኔታውን ቀድሞ እንዳልነገራቸው በአንክሮ ያዳምጡታል እንጂ "በዚህ ቀን መጥተህ ነግረኸኝ አልነበረም ወይ በል አሁንም የተለየ ነገር የለምና መጥተህ ሌላ ባለጉዳይ ላነጋግር" አይሉትም ነበር፡፡ ምናልባት ይህ ባሕርያቸው እንዲሁ በሩቁ ስንሰማው ቀላል ይመስለናል፡፡ ነገር ግን ሁላችንም ብንሆን በሥራ ላይ እናውለው ብንል አንችልም፡፡

ሌላው ቀርቶ አንድ ሰው ተጣልቶኛል ብሎ ያሰበ እንደሆነ ወይም ደግሞ እርሳቸው ተጨነውኝ ምንም ለማደግ አልቻልኩም ብሎ ቢል ወደ እርሳቸው አቅርበው ይሾሙታል፡፡ በእርሳቸው ደረጃ የማይችሉ ከሆነ ወደ ጃንሆይ አቅርበው ያሾሙታል፡፡ በወቅቱ በአገር ላይ አሉ የሚባሉ ባለሥልጣናት ፓትርያርኩና ንጉሡ ነበሩ፡፡ ቅዱስ አባታችን ግን ያን ያህል የተጋነነ ስሜት አልነበራቸውም፡፡

በቋንቋውም በኩል እንግሊዝኛ፣ ጣሊያንኛና ግሪክኛ እንዲሁም አረብኛና ዕብራይስጥ ለምርምር ያህል ይችሉ ነበር፡፡ አስታውሳለሁ በ1965 ዓ.ም. በአሜሪካ መንግሥት ተጋብዘው ወደዚያ ሄደው ነበር፡፡ ለጉብኝቱ ቅዱስነታቸው በአፍሪካ የመጀመሪያው ፓትርያርክ ነበሩ፡፡ በወቅቱ የአሜሪካ ጋዜጦች "The black Pope" በሚል ርእስ ባቀረቡት ሰፊ ዘገባ አሜሪካ መግባታቸው ታውቆ በአገሪቷ በትልቅ አክብሮትና አቀባበል ነበር የሚንቀሳቀሱት፡፡ በየስቴቱ ምሁራንና ሌሎች ታላላቅ

ሰዎች እየተቀበሉ ያስተናግዷቸው ነበር፡፡ ቅዱስነታቸው ከሰዎች ጋር ይወያዩና ስለ ቤተ ክርስቲያናችን ማንነት በሚያስደንቅ ሁኔታ ያስተምሯቸው ነበር፡፡ አስታውሳለሁ በተለይ በኒዮርክ ከተማ ኮሎምቢያ ዩኒቨርስቲ በተደረገላቸው የራት ግብዣ ላይ ከነበሩት የዩኒቨርሲቲው ታላላቅ ምሁራን ለቀረቡላቸው ጥያቄዎች የሰጡት መልስና ትምህርት ማንነታቸውን በሚገባ ያሳየ ነበር፡፡ ጥልቅና ምጡቅ በሆኑ መልሶቻቸውና ትምህርታቸው በእሳቸው አማካኝነት ኢትዮጵያ ማንና የእነማን አገር እንደሆነች በሚገባ ማወቃቸውን በዚያው ወቅት ለቅዱስነታቸው በአክብሮት ገልጠውላቸው ነበር፡፡

በእውነቱ ቅዱስነታቸው በወገኖቻቸው ብዙ ያልታወቁ እንዲሁ ብቻ በአገራቸው በቃ መንፈሳዊ አባት፣ መምህር ናቸው በሚል ብቻ ሳይታወቁ ያለፉ አባት ነበሩ፡፡ ዛሬ እንደ እርሳቸው ያለ ትዕግሥተኛና አርቆ አስተዋይ የለም፡፡ ወደፊት ስለሚኖረው የቤተ ክርስቲያንንና ልጆቿ ሁኔታ ያውቁ ነበር፡፡ ወደፊት የቤተ ክርስቲያን ልጆች ዘመናዊ የእውቀትንና የአመለካከት ልዩነት እንደሚፈጠር በሚገባ ያውቁ ነበር፡፡ ታዲያ መለያየት የቤተ ክርስቲያን ጠላት እንደመሆኑ ልዩነቱ እንዳይኖር ለማድረግ በወጣቶችና በካህናት መካከል እንደ ድልድይ በመሆን የሚያገለግሉ ዘመናዊውንም ሆነ ጥንታዊውን የቤተ ክርስቲያን ትምህርት የቀሰሙ ወጣት ሊቃውንት የሚፈልቁበትን መንፈሳዊ ኮሌጅ እንዲቋቋም አድርገዋል፡፡ እንግሊዝኛ መናገር የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ እውነተኛ የቤተ ክርስቲያን ልጅ አይደለም በሚባልበት ዘመን የነበረውን ጫና ሁሉ አሸንፈው ካህናት ቋንቋውን አውቀው እንዲሁ አይዞህ ልጄ በማለት ብቻ የማይመለሰውን ትውልድ እንዲጠብቁ ማድረጋቸው በእውነቱ የሚያስመሰግናቸው ነው፡፡

ሌላው ቤተ ክርስቲያን የነበራትን ርስት ጉልት ይዛ እንደማትቀይ፣ መሬት የመንግሥት እንደሚሆን በሩቁ ያዩ አባት ነበሩ፡፡ ስለዚህ ያ ጊዜ ሲደርስ ቤተ ክርስቲያን ችግር ላይ እንዳትወድቅ ምእመናን ቤተ ክርስቲያናቸውን እንዴት እንደሚያገለግሉ እነርሱም እንዴት እንደሚገለገሉ በጥቅሉ የወደፊቷ ቤተ ክርስቲያን ምእመናንን ማስተዳደር የምትችልበትን ሕግ /ቃለ ዐወዲ/ እንዲዘጋጅ ያደረጉ አባት ነበሩ፡፡ ይህ ቃለ ዐወዲ ቤተ ክርስቲያን በመካከል የነበረባትን ፈተና አልፋ እንድትቆይና ዛሬ እኛ እንድንረከባት አድርጓል፡፡

ከዚህም ሌላ ቤተ ክርስቲያናችን ለብቻዋ በአፍሪካ ክፍለ ዓለም ብቻ ተወስና መኖር እንደማትችል በማወቅ የዓለም አብያተ ክርስቱያናት ኅብረት አባል እንድትሆን አድርገዋል፡፡

በእውነቱ ልጆቼ ስለቅዱስነታቸው ሥራና የግል ሕይወት ብዙ ማለት ይቻላል፡፡ የሆነው ሆኖ አባታችን መናኝ ነበሩ፣ ትዕግሥተኛ ነበሩ፣ ሁሉንም በአስተዋይነት የሚመለከቱ ታዋቂ ምሁር ነበሩ፡፡

*ሐመር፦* ከእኒህ ታላቅ የቤተ ክርስቲያን አባት ተምሬዋለሁ ብለው ከሚያስቡዋቸው ነገሮች ዋና ዋናዎቹን ቢገልጹልን?

*ቅዱስነታቸው፡-* አይ ልጆቼ ከእኒህ መጽሐፍ ቅዱስን በሕይወታቸው ከተረጎሙ አባት ብዙ ብዙ መማር ይቻል ነበር፡፡ ሕይወታቸው በሙሉኮ አስተማሪ ነበር፡፡ የሆነው ሆኖ የቅዱስነታቸውን ጠባይ ሙሉ በሙሉ ነሥቻለሁ ባልልም አሁን በትንሹ የምንቀሳቀስበትን ያህል ከእሳቸው ወስጃለሁ፡፡ ይኸውም ምንም ዓይነት ነገር ቢያጋጥም በዓላማ ጸንቶ መገኘት፡፡ አንድ ሰው ባላደረገው ነገር መጨነቅና ማሰብ እንደሌለበት፣ መጨነቅና ማሰብ ያለበት ክፉ ነገር እንዳይሠራ መሆኑን ተምሬአለሁ፡፡

*ሐምር፡-* በነገረ መለኮት ትምህርት የሁለተኛ ዲግሪና በፍልስፍና ትምህርት የዶክትሬት ዲግሪ ባለቤት ነዎት፡፡ ለመሆኑ እነዚህን ሁለት የእውቀት ዘርፎች /ፍልስፍናንና ነገረ መለኮትን/ እንዴት አጣጥመው ውጤታማ ሊሆኑ ቻሉ?

*ቅዱስነታቸው፡-* በእርግጥ እንደተባለው የፍልስፍና ትምህርት ተምሬ ያለሁ፡፡ ነገር ግን የተማርኩት ፍልስፍና ከነገረ መለኮት ትምህርት ጋር የሚጋጭ አይደለም፡፡ የተማርኩት የዓለሙ ፈላስፎች እምነታችንን ለመንቀፍም ሆነ ለመተቸት ሲመጡ የእነሱን አካሄድ ተረድተን ለመቋቋም እንድንችል በአባቶች ተተንትኖ የተቀመጠውን የክርስትናውን የፍልስፍና ትምህርት ነው፡፡ ይህ ትምህርት ስለ ህልዎተ እግዚአብሔር የሚገልጽ፣ ስለዓለም አፈጣጠር የሚያስረዳ ትምህርት ነው፡፡ በ3ኛውና 4ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የነበሩ ግሪካውያንና ሮማውያን ፈላስፎች ስለ እግዚአብሔር መኖር ተጻራሪ የሆነ ፍልስፍናዊ ትምህርት ይሰጡ ነበር፡፡ በወቅቱ የነበሩ አባቶችም የእነዚህን ፈላስፎች ትምህርት ለመመከት ስለ እግዚአብሔር መኖርና ሌሎች ተያያዥ ነገሮችን የሚያስረዳ መንፈሳዊ የፍልስፍና ትምህርት አዘጋጁ፡፡ ስለዚህ እኔም በውስኗ አቅሜ ይህንን የአባቶችን ትምህርት አጥንቼ ለዚህ በቅቼአለሁ፡፡ እንዴት አስታረካቸው ለሚለውም ድሮም የተለያዩ አልነበሩምና እነሱን በአንድነት እስኪጀቸዋለሁ፡፡

*ሐመር፡-* እስከ አሁን ባሳለፉት የሕይወት ዘመንዎ እጅግ ያዘኑባቸውና እጅግ የተደሰቱባቸው አጋጣሚዎች ካሉ ቢገልጹልን?

*ቅዱስነታቸው፡-* የተደሰትክበት ላላችሁኝ በአንድ ወቅት ተደስቼበት ያለፈ ሳይሆን ሁል ጊዜ ቢያስደስተኝ የሚኖር ነገር አለ፡፡ ይኸውም በሃይማኖታቸው የጠነከሩ፣ በዓላማቸው የጸኑ፣ በእግዚብሔር የታመኑ ቤተሰቦቼን መንገድ ተከትዬ በመጓዝ ላይ በመሆኔ ነው፡፡ ይህ ዓለም አንድ ቀን ይበራል፣ ሌላ ቀን ደግሞ ይጨልማል፣ አንድ ቀን ሀብት ይዞ ይመጣል፣ ሌላ ቀን በድኅነት ይመጣል፣ አንድ ቀን ደግሞ የሚኮሩ የሚመኩበትን ሁሉ ገፎ ባዶ ያስቀራል፡፡ ስለዚህ ወላጆቼ እኔም በማያስመካው ሐላፊ ዓለም መመካትን ትቼ በእግዚአብሔር እንዳምን ስላደረጉኝ እግዚአብሔርን በማመስገን ወላጆቼን ደግሞ በማድነቅ እደሰታለሁ፡፡

ያዘንክበት ለተባለው ግን መልሴ ጨርሶ አዝኜ አላውቅም የሚል ነው፣ በዚህ ዓለም ጨርሶ የሚያሳዝን ጨርሶ ተስፋ የሚያስቆርጥ ነገር አለመኖሩን በማስተዋል እራስን ወደሚፈለገው ቦታ መምራት ይገባል፡፡ ማዘን ቢኖርብኝ ለሰባት ዓመታት በዓለሙ እስር ቤት ስቆይ አዝን ነበር፡፡ ነገር ግን የ ቆይታዬ ያዘንኩት እንዳይመስላችሁ፡፡ የተደሰትኩት፣ ያገለገልኩበት ሕይወት ነበር፡፡

ምናልባት ለወዲያው እንዴት እታሰራለሁ ብዬ ጠይቄ ነበር፡፡ ነገር ግን ወዲያውኑ ያ ሕይወት እኔም የምጠነክርበት ሌሎች ወንድሞቼም የሚጠሩበትና የሚጠነከሩበት ወቅት መሆኑን ተረድቼ ሐዋርያዊ ግዴታዬን ነው መወጣት የጀመርኩት፡፡ በእውነቱ ይኸን በወቅቱ አብረውኝ ነበሩ ሁሉ ያስታውሱታል፡፡ ጓደኞቼ ሲያዝኑ በማስተማርና በመማር ለቤተሰቦቻቸው ደብዳቤ በመጻፍ ያጽናናሁበት እኔም የተጽናናሁበት ወቅት ነበር እንጂ አስቦ ለማዘን ጊዜ አልነበረኝም፡፡

*ሐመር፡-* ከዕለት ወደ ዕለት እየጨመረ የመጣው የንዋያተ ቅድሳት ዝርፊያን በሚመለከት ቤተ ክርስቲያን እየወሰደች ያለውን ርምጃ ቢገልጹልን?

*ቅዱስነታቸው፡-* እውነት ነው ብዙዎቹ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሀብት የሆኑት ንዋያተ ቅድሳት የበለጠ መዘረፍ የጀመሩት ከቅርብ ጊዜ ጀምሮ ነው፡፡ ይህም የሆነው እንደ እኔ እምነት በውስጣዊና በውጫዊው ምክንያቶች ነው፡፡ ውስጣዊው ምክንያት እንደምን ነው? ብትሉኝ ጊዜ ያመጣው ሁኔታ ነው፡፡ ምናልባት በቤቶቹ ማርጀት፣ በጠባቂዎቹ የደመወዝ ማነስ ዝርፊያ ሊባባስ ቻለ ሊባል ይችላል፡፡ ነገር ግን ያ በእውነት ተቀዳሚ ምክንያት ሊሆን አይችልም፡፡ የድሮዎቹ ንዋየተ ቅድሳት በየትኛው ዘመናዊ መሣሪያ ነው ሲጠበቁ የነበረው? በየትኛውስ ዘመናዊ ሙዝየም ነበር የተቀመጡት? በደካማዎቹ

አባቶቻችንና በቀለሷት ጎጆ አልነበረም የወር ደሞዝ፣ ጉርሻ ሳይሰጣቸው እነሱም ሳይፈልጉ በደረቅ ጠፍር ወገባቸውን አስረው በሚሊዩን የሚቆጠር ገንዘብ የሚያወጣ ዕቃ ብድግ አድርጎ ወስዶ ሸጦ መበልጸግ ሲቻል ያንን ዕቃ ይዘው ነው የቆዩት፡፡

በተለያዩ ጊዜያት እንደ አሁኑ አይሁን እንጂ የተለያዩ ቱሪስቶች ሲመጡ ነበር፡፡ ታዲያ በየገዳማቱ ሲሄዱ በቀላሉ የመንፈስ ጽናት የነበራቸው ገዳማውበያን ናቸው፡፡ ማንም ገንዘብ አለኝ ብሎ እንደፈለኩ ልግባ ቢል አያስገቡትም፣ ሃይማኖት አላቸው፤ የሚከላከሉበት መሣሪያም ሆነ ሌላ ኀይል አልነበራቸውም፡፡ መሣሪያቸው ሃይማኖታቸው ነበር፡፡ አሁን ግን ይህ ጽናት የቀነሰ ይመስለኛል፡፡

ሌላው የጥንቶቹን ንዋያተ ቅድሳት የሚጠብቁ በገዳም ያሉት መነኮሳት ብቻ አልነበሩም፣ በአካባቢያቸው የነበሩ ምእመናንም በንቃት ይጠብቁ ነበር፡፡ ምክንያቱም ያ በገዳም ያለው ንዋይ የእነሱ ቆይቶም የልጆቻቸው መሆኑን በሚገባ ያውቁ ነበርና ነው፡፡ በአሁኑ ጊዜ ግን ያ ዓይነቱ የመንፈስ ጥንካሬ ጎልቶ አይታይም፡፡ በውጫዊ ምክንያት ሊጠቀሱ ከሚችሉት ምክንያቶች ደግሞ የአገራችንን ከፍ ከፍ ማለት፣ ታሪኳ፣ የዕውቀትና የሥልጣኔ ምንጭነቷ በዓለም ሕዝብ ዘንድ እንዲታወቅ የማይፈልጉ ክፍሎች መብዛት ነው፡፡ የኢትዮጵያ ታሪክ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ፣ የኢትዮጵያ ሀብት የቤተ ክርስቲያን ሀብት በመሆኑ ቤተ ክርስቲያንን ለማዳከም የሚያደርጉት ነው፡፡ ኢትዮጵያ ስትጠራ በቅድሚያ የምትጠራው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በመሆኗ ኢትዮጵያን ለማዳከም ይኸውና የቤተ ክርስቲያን ደብዛ ለማጥፋት በመዝረፍ ላይ ይገኛሉ፡፡ የቤተ ክርስቲያን በእሷም በኩል የሀገር ሀብት የሆኑት ቅርሶቻችን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ እየተወሰዱ በዓለም ላይ ተበትነዋል፡፡

እንግዲህ ይህን ሁሉ በማወቅ እናንተ ምን እየሠራሪችሁ ነው? ቢባል እኛማ ባለን አቅም እየለመንን የፈረሰውን መጠገን፣ እባካችሁ እንደዚህ በእንጨት ላይ እንጨት አነባብረን እናስቀምጠው እያልን ደካሞች አባቶችን እንመክራለን፡፡ ምእመናንም በየአጥቢያቸው ያሉ ንዋያተ ቅድሳትና ታሪካዊ ቅርሶች ከአባቶቻቸው የወረሷቸው ጥሪቶች መሆናቸውን አውቀው እነርሱም ተረክበው ለልጆቻቸው እንዲያስረክቡ እናስተምራለን፡፡ ምእመናንም በየአጥቢያቸው ያሉ ንዋያተ ቅድሳትና ታሪካዊ ቅርሶች ከአበቶቻቸው የወረሷቸው ጥሪቶች መሆናቸውን አውቀው እነርሱም ተረክበው ለልጆቻቸው እንዲያስረክቡ እናስተምራለን፡ ፡ ይህ ግን በቂ አይደለም፡፡ እኔ እንደማየው በየማእከሉ እንደ አቅማችን ዘመናዊ ሙዚየሞችን በመሥራት ለእነሱም መንገዶችን በመዘርጋት ሀብታችንን ከጥቅም ላይ እንዲውል ማድረግ አለብን፡፡ ለዚህም አጠቃላይ የኢትዮጵያ ሕዝብና መንግሥት መትጋት አለባቸው፡፡ ከኢትዮጵያ ጋር ተመሳሳይ ችግር የነበራት ሩሲያ ባደረገችው ሰፊ ጥረት በዚያ ሀገር በነበረው የኮሙኒስት መንግሥት ፈርሶ የነበረው ትልቅ ቤተ ክርስቲያን በአሁኑ መንግሥት በዋናው ከተማ አንድ ቢሊየን ዶላር በፈጀ ወጭ ተሠርቶ ለአገልግሎት ውሏል፡፡ በዚያው ዘመን ተበትነው የነበሩ ቅርሳ ቅርሶች ሁሉ ተሰባስበው በአንድትልቅ ዘመናዊ ሙዚየም እንዲቀመጡ ለማድረግ መንግሥት ሌላ 18 ሚሊየን ዶላር ተጨማሪ ርዳታ ሰጥቷል፡፡

እኔ በመሠራት ላይ ያለውን ቤተ ክርስቲያን በሥራ ምክንያት ሄጀ በነበረ ጊዜ አይቼዋለሁ፡፡ እንደነገሩኝ ከሆነ ለሥራ ማስኬጃው የሚያዋጡ ያሉት ክርስቲያኖች ብቻ አይደሉም፡፡ ኮሙኒስቶችም ያዋጣሉ፤ የሀገራቸው ታሪክ የሀገራቸው ሀብት ነውና፡፡ ስለዚህ በመናኛ አያያዝ በየቦታው የተወሸቁት ሀብቶቻችን ንዋያተ ቅድሳት ብዙዎች ናቸውና ሁሉም ኢትዮጵያዊና መንግሥት ቅርሶቻችንን ለመንከባከብ መትጋት አለበት፡፡ በእውነቱ ዘመኑ በፈጠረው ቴክኖሎጂ ተጠቅሞ ሀብትን ማደርጀት ይገባል፡፡ ነገር ግን ከዚያ የበለጠ ሀብት በእጃችን አለ፡፡ እነዚህ ሀብቶቻችን በአግባቡ ተሰብስበው፣ በአግባቡ ማእከላዊነት

ባላቸው ቦታዎች ቢከማቹ በእነሱ አማካኝነት የምናገኘውን ገንዘብ አፍሰንም አንጨርሰውም፡፡ ስለዚህ ሕዝቡ ንብረቱ እንዳይባክንበትና እንዳይቀሰጥበት በጥንቃቄ መያዝና መንከባከብ አለበት፡፡

የኢትዮጵያ ታሪክ በቅርስነትና እንዲሁም በጽሑፍ የሚገኘው በእነዚህ ገዳማት ነውና መንግሥትም ጉደዩን ቸል ሳይል ለእንክብካቤያቸው የበለጠ ጥረት ማድረግ አለበት፡፡ እነዚህ ገዳማት ሸለቆ ውስጥ ወይም ተራራ ላይ ናቸው ወይም ደግሞ ከመንደሩ ራቅ ያሉ ናቸው፡፡ ስለዚህ መጋቢ መንገዶች ያስፈልጓቸዋል፡፡ ጎብኝዎች መጥተው ያንን የሚያኮራንን ታሪክ መጎብኘት መቻል አለባቸው፡፡ ይኼንን ነገር ክልሎች ሁሉ በየቦታቸው ላሉ ገዳማትና ታሪካዊ ቦታዎች በጀት የሚሠሩላቸው መሆን አለበት፡፡ ሕዝቡን ወክለው የተቀመጡት ተወካዮችም ሊመክሩበት፣ ሊተቹበት ይገባሉ፡፡ ልማት በሁለቱም አቅጣጫ ሲሆን ነው ውጤታማ የሚሆነው፡፡ ስለዚህ ቤት የሚጠበቀው በባለቤት ነውና ለንዋየተ ቅድሳት ዝርፊያም ሆነ የተዘረፉትን ለመመለስ ቤተ ክርስቲያን፣ ምእመናንና መንግሥት ይትጉ እላለሁ፡፡

*ሐመር*፡- በአሁኑ ወቅት ያሉት ሁለቱ ዘመናዊ የቤተ ክርስቲያን የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ማለት ቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅና የሰዋሰወ ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ ከፍተኛ መንፈሳዊ ትምህርት ቤት የሚሰጡት ትምህርቱ ጥራትና ብቃት ምን ያህል ነው ይላሉ?

*ቅዱስነታቸው*፡- እርግጥ ነው አርቆ አስተዋይ አባቶቻችን የከፈቱልን ሁለት የከፍተኛ ትምህር ተቋማት አሉን፡፡ በእነዚህ ተቋማት በቤተ ክርስቲያን አድገው ዶግማዋን ትምህርተ ሃይማኖትን ቀኖዋንና ባሕሏን ያወቁ ወጣት ሊቃውንት ይዘውት የመጡትን ዕውቀት ለዘመኑ ትውልድ በቋንቋውና በሚፈልገው መንገድ እንዴት ማቅረብ እንደሚችሉ ይማራሉ፡፡ የሆነው ሆኖ እነዚህ ያሉትም ሆነ ወደፊት የሚኖሩት ዋና ዋናዎቹ የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ምንጮች ባለመኖራቸው በትምህርት ተቋማቱ ማነስ ሊቃውንት አልነበሩም ወደፊትም በብዛት አይገኙም ማለት አይቻልም፡፡ የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን በዜማ፣ በቅኔ፣ በትርጓሜ መጻሕፍት በድርሰትና በስብከት በዓለም መድረክ እንድትታወቅ ያደረጓት ሊቃውንት የተገኙት ከጥንታውያን ገዳማት ነው፡፡ ስለዚህ እነዚህ ሁለት ትምህርት ቤቶች ቢኖሩም ዋና ዋናዎቹ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማቶችን ገዳማትና አድባራት በመሆናቸው የዘመናውያኑ ትምህርት ቤቶች ቁጥር ማነስ ቤተ ክርስቲያንን የሊቃውንት ድሃ አያደርጋትም፡፡

*ሐመር*፡- በአሁኑ ወቅት ሌሎች የእምነት ድርጅቶች የቤተ ክርስቲያንን ልጆች ለመውሰድ ከሚያደርጉት እንቅስቃሴ አንፃር ምን መደረግ አለበት ይላሉ?

*ቅዱስነታቸው*፡- በእውነቱ በሀገራችን መናፍቃን እንደፈለግን እንሰበክ ሊሉ የቻሉት በቤተ ክርስቲያን ሰዎች መዘናጋትና በአንድ አንድ አማንያን ደካማ ጎን እየገቡ ነው፡፡ መናፍቃን በዞ፣ ቤታችንን ሞሉት እንደዚህ ቢባል በግድየለሽነት ወይም ደግሞ ባለማወቅም ሊሆን ይችላል፡፡ ሀይማኖት የሚጠበቀው አኮ ሁሉም ሃይማኖቱን አጥብቆ ሲይዝ ነው፡፡ ስለዚህ ቤተ ክርስቲያንን ከመናፍቃኑ እንቅስቃሴ ለመታደግ ሁሉም ተዘጋጅቶ መገኘት አለበት፡፡ የቤተ ክርስቲያን አባቶች ለልጆቻችን ተገቢውን ትምህርት በሚገባቸው መንገድ ለማስተማር መትጋት አለብን፡፡ ምእመናን እንዲገባቸው አድርጎ ትምህርት ከተሰጡ የማይቀበሉበት ምክንያት የለም፡፡ ስለዚህ ልጆቻችን ያፈነገጡት ባለ መማራቸው ነውና ልናስተምራቸውና ልንጸልይላቸው ይገባል፡፡ በእውነተኛይቱ እምነት ያሉትን ልጆቻችንን ደግሞ ምንም እንኳ የቤተ ክርስቲናቸው ፍቅር ከቤታቸው ባያወጣቸውም ማንነቷን አውቀው ፍቅራቸውን እንዲያጸኑ ልናስተምራቸው ይገባል፡፡

ዘመቻው በቤተ ክርስቲያን ላይ ነውና ሰበካ ጉባኤያት የምእመናን እንደመሆናቸው ማስተማርና ለቤተ ክርስቲያናቸው ዘብ እንዲቆሙ መምከር አለባቸው፡፡ በመካከላቸው መናፍቅነት የተሰማቸው ቢኖሩ ምንድነው ችግሩ? ብሎ መምከር አለባቸው፡ ፡ ይህ የጌታ ትምህርት ነው፡፡ ያጠፋን ሰው መጀመሪያ መምከር ማስመከር ይገባል፡፡ እንቢ ላለ ግን እንደ አባቶቻችን ሥርዓት ወገንነቱን እንዲለይ ማድረግ ነው፡፡

እኔ ብዙ ጊዜ ከምእመናን ጋር ስገናኝ አዘውትሬ የምናገረው ነገር አለ፡፡ ልጆቻችን በሌሎች ትምህርት ቤቶች ነው የሚማሩት፡፡ ለምንድን ነው በየአጥቢያችን ዘመናዊ ትምህርት ቤቶችን የማናቋቁመው? እንደ እኔ ሰበካ ጉባኤ ቅድሚያ ሰጥቶ መሥራት ያለበት ይህንን ነው፡፡ ካስተባበሩት ሕዝቡ ከዚያ የበለጠ ሥራ መሥራት ይችላልና እናስተባብረው፡፡ በእውነቱ ይህንን ጥሪ ተቀብለው ተግባራዊ እያደረጉ ወይም ሥራ እየሠሩ ያሉ ጥቂት አድባራት ብቻ ናቸው፡፡ ሌሎችስ? ይህ እኮ በእጃችን ያለ ነገር ነው፡፡ ሕፃናት ነገ የሚዘገይባቸው ሰዎች ናቸውና ለምቾታቸው ዛሬውኑ ልንንቀሳቀስላቸው ይገባል፡፡

ወላጆች የልጆቻቸው መምህራን ናቸውና የቤተሰብ ጉባኤ ማዘጋጀት የተማሩትን ትምህርት ለልጆቻቸው በወላጅነት ቋንቋ ማስተማር አለባቸው፡፡ እያንዳንዱ ቤተሰብ ከጉባኤ መልስ በተማረው ትምህርት አጀንዳነት መወያየት አለበት፡፡

*ሐመር*፡- ቤተ ክርስቲያን ከመንግሥት የምታገኘው ድጎማ እንደቀነሰ ይታወቃል፡፡ ከዚህ አንጻር ቤተ ክርስቲያን ለወደፊቱ የገቢ ምንጭ ይሆናሉ ብላ ከያዘቻቸው ዕቅዶች ዋና ዋናዎቹን ቢጠቅሱልን?

*ቅዱስነታቸው*፡- በመሠረቱ እንደሚታወቀው ቤተ ክርስቲያን እጅግ ብዙ ከራሷ አልፎ ለሌሎች የምትረዳው ሀብት ነበራት፡፡ ነገር ግን የደርግ መንግሥት የነበረውን ዓመታዊ ገቢዋን በመቁረጥ 4 ሚሊዮን ያህል ብር ብቻ ነበር የጣለላት፡፡ እና ቢያንስ ራሷን በራሷ እንድታስተዳድር የቤተ ክርስቲያኗ የሆኑ የከተማ ቤቶች በሙሉ እንዲመለሱ ያሁኑ መንግሥት ወሰነ፡፡ በውሳኔውም መሠረት ከመቶ አሥር ፐርሰንት ያነሰ ቢመለስም ከዘጠና ፐርሰንት በላይ ያለው ገና ያልተመለሰ ነው፡፡ የአገርን ታሪክ እየመዘገበች ስታስተምር ለኖረች፣ አሁንም በማስተማር ላይ ላለች፣ ወደፊትም ለምታስተምር ሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያን ሀብቷን መመለስ እጅግ ቀላል ነገር ነውና በዚህ አጋጣሚ ቤቶቻችን ተጠቃለው እንዲመለሱ የሚመለከተውን ክፍል አደራ እላለሁ፡፡

ስለዚህ በገቢ ምንጭነት የእነዚህን ቤቶች ኪራይ ብንጠቀም ራሳችንን እንችል ነበር፡፡ ሌላው ሰበካ ጉባኤያት ተጠናክረው ምእመናንን በማስተማር አሥራት በኩራታቸውን እንዲያወጡ በማድረግ የቤተ ክርስቲያናቸውን እንቅስቃሴ በገንዘብ እንዲደግፉ እናደርጋለን፡፡ በተረፈ በርካታ ቅዱሳት መካናት አሉን፤ ብርቅና ድንቅ የሆኑ ንዋያተ ቅድሳቱም በውስጣቸው አሉ፡፡ እነዚህ የእምነትና የእውቀት ምንጮች በሚገባ ታድሰው የገቢ ምንጭ የሚሆኑበትን መንገድ በማፈላለግ ጥረት እናደርጋለን፡፡ ገዳማቱም መብታቸው ተጠብቆ መሬት እንዲያገኙ ሆኖ ራሳቸውን እንዲያስተዳድሩ ለማድረግም አቅደናል፡፡ እንግዲህ እኛ የአቅማችንን እንሠራለን፡፡ እግዚአብሔር እንደሚረዳንም እናምናለን፡፡

*ሐመር*፡- በዘመናችን የኤድስ በሽታ የዓለምን ሕዝብ በሚያሰቅቅ ሁኔታ እየፈጀ ይገኛል፡፡ ይህን በሚመለከት ቤተ ክርስቲያን ልጆቿን ከበሽታው ለመታደግ ምን እያደረገች ነው?

*ቅዱስነታቸው*፡- ይህ ጥያቄ ወቅታዊ ጥያቄ ነው፡፡ ሁላችሁም እንደምታውቁት ይህ በሽታ የተፈጠረው ከኀጢአት ብዛታ የተነሣ ነው፡፡ ለዚህ ደግሞ መጻሐፍ ቅዱስ ምስክር ነው፡፡ ቅዱስ መጽሐፍ ቀርቶ ራሱ ሳይንሱ ይደግፈዋል፡፡ ያልቀበጠ

በበሽታው አይያዝም። የኀጢአት ሥራ ውጤቱ ሞት ነው። ሌላ ነገር አይደለም። አዳምና ሔዋን እግዚአብሔር ይወዳቸው እነሱም ይወዱት ነበር።

ነገር ግን ሕግ በመተላለፋቸው ተጣሉ። ስለዚህ እንዲህ ያለ ሕግ መተላለፍ ከእግዚአብሔር ጋር ያጣላል፤ በራስ ላይም መቅሰፍት ያመጣል። በመሆኑም በኀጢአት የመጣ ቅጣት ማጥፊያው ንስሐ በመግባት ነው። ንስሐ መግባት ማለት ምን ማለት ነው? ኀጢአት አለመሥራት ሕግ አለመተላለፍ ማለት ነዋ።

በዚሁ በሽታ ምክንያት የዘመኑ ሊቃውንት ብዙ ብዙ ይናገራሉ። ሊቃውንቱ ስለበሽታው መስፋፋት ዕለት ዕለት ይናገራሉ። በዚህ እኔም እስማማለሁ። እውነት ነው ልጆቻችን ገና ብቅ ብቅ ከማለታቸው እየተቀጩ ነው። መፍትሔ ይሆናል በሚሉት ላይ ግን እኔ አልስማማም። ዛሬ እየተሰጡ ያሉት ምክንያቶችና መፍትሔዎቻቸው በሽታው ግን ከመሮጡ፣ ከመከሰቱ፣ ብዙ ሰዎችን ከማጥመዱ የታቀበበት ጊዜ የለም። እርግጥ ሊቃውንቱ የጭንቀታቸውን ያህል መፍትሔ ይሆናሉ ያሉዋቸውን ነገሮች መሰንዘራቸው አያስወቅሳቸውም። ነገር ግን ይህ ይበጃል ያሉት መፍትሔ ሰዎችን እንዳልረዳ ዐውቀው ሌላ መንገድ መቀየስ አለባቸው። ይኸውም ከሃይማኖት አባቶች ጋር በመተባበር ሕዝቡ በሕግ በሥርዓት እንዲኖር ማስተማር ይጠበቅባቸዋል።

ስለዚህ ጉዳዩን በባለቤትነት የያዙ ክፍሎችም በዓመት ብዙ ሚሊዮን ብር ሲያፈሱ እናያለን፤ እንሰማለለን። ሥራቸው ሙሉ በሙሉ ውጤት አልባ ነው ለማለት ባይቻልም ይኸው በሽታ ታየ ከተባለ ወደ 20 ዓመታት ተጠጋው የሚያስደስት ውጤት አናይም። በሽታውም ከመሮጥ አልቆመም። ነገር ግን በቤተ ክርስቲያናችን ሕግና ሥርዓት መሠረት በወንድና በሴት መካከል ያለው ግንኙነት ወላጆች ሳይፈቅዱ ቤተ ክርስቲያንም ሳታውቀውና ሳትፈቅድ ከሆነ ኀጢአት ነው። ደግሞም በሌሎች ሀገራት አይታወቅም እንደሆነ እንጂ ራስን በድንግልና አጽንቶ መኖር፣ በሕግ ጸንቶ መኖር፣ ለሕግ የሚበቃበትን ጊዜ በተስፋ መጠበቅ አባቶቻችንና እናቶቻችን ያቆዩልን ነው። እግዚአብሔር የፈቀደላቸውን እስከሚያገኙ ድረስ ያላስቀመጡትን ወይም ደግሞ ያላስቀመጡላቸውን አያነሡም ነበር። የእኅቶቻቸውንም ክብር የሚጠብቁ ወንድሞቻቸው ነበሩ። ይህንን የሚያስጠብቁ ደግሞ ወላጆች ናቸው። በመምከር፣ በመቆጣትና በመቅጣት። አሁን አሁን ግን ይህን ጉዳይ ልጆቻችን እየዘነጉት የመጡ ይመስለኛል። ይህ የሆነበት ምክንያት ደግሞ በራሳችን በመጣ ግፊት ሳይሆን የውጭ ሀገሩ ባሕል ግፊት ነው። እነሱን እንመስላለን፣ እንሆናለን በሚል በመናኛ አስተሳሰብ ነው። ስለዚህ ልጆቻችን ሊማሩ፣ ሊመለሱ ይገባል። በሕግ መተላለፍ የመጣን መጥፎ ነገር ማስቆም የሚቻለው ወደ ሕግ በመግባት ነው። በመሆኑም ላለፈው ይቅር እንዲለን ለወደፊቱም እግዚአብሔር እንዲጠብቀን ንስሐ መግባት አለብን። እሮጣለሁ፣ አብዳለሁ እኔን ግን ፈውሱኝ አይሆንም። አንድ ሰው ከያዘው የሥጋም ሆነ የነፍስ ደዌ መፈወስ ካለበት ከሚፈወሰው ሰው ጋር መጨነቅ መፍትሔውንም መሻት አለበት። በቅዱስ ወንጌላችን አንድ ትልቅ ትምህርት አለ። 38 ዓመት መፃጉዕ ሆኖ የኖረውን ሰው ጌታ ሊያድነው ፈልጎ ወደ መጠመቂያው ወረደ። ጌታም ይህን ሕመምተኛ እንዳየው አንድ ለሁሉም የሚሆን ጥያቄ ጠይቆት ነበር። ይኸውም "አንተ ሰው ልትድን ትወዳለህን" የሚል ነበር። ጌታችንና መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሽተኛው ሊድን የሚፈልግ መሆኑን አጥቶት አይደለም። ነገር ግን ድኅነት የሚገኘው ፈቃደኛ ሆነው ሲገኙ ብቻ መሆኑን ለማጠየቅ ነው። ስለዚህ ወጣቶች የአባቶቻቸውን ምክርና ተግሳጽ እየተቀበሉ ራሳቸውንም ሆነ ሌሎችን መጠበቅ አለባቸው።

አገራችን ከትውልዱ ብዙ በምትጠብቅበት ጊዜ በቸልተኝነት ትውልዱ እያለቀ ነውና አባቶች አዘውትረን ማስተማር አለብን። በዚህም ላይ ካህናት ሊቃውንትና ሰባክያነ ወንጌል ልጆቻቸውን የመጠበቅ ግዴታ የታከለበት ሓላፊነት አለባቸው።

ሕዝባችን ሃይማኖተኛ ስለሆነና ነገሩ ደግሞ የሃይማኖት መልእክት የሚያስፈልገው በመሆኑ እኛ ዝም ማለት የለብንም፡፡ በእግዚአብሔር እንዳንወቀስ ይህንኑ የተጠራንበትን ዓላማ ማሟላት አለብን፡፡ እንዲህ መሆን አለበት ስል ግን በቤተ ክርስቲያን እስካሁን ምንም ዓይነት ሥራ አልተሠራም ብዬ አይደለም፡፡ ቤተ ክርስቲያን ለነገሩ ትኩረት ሰጥታ በልማት ኮሚሽን በኩል ራሱን የቻለ ኮሚቴ አቋቁማ ካህናት ግንዛቤያቸው ሰፍቶ ምእመናንን እንዲያስተምሩ በማስተማርና ሌሎች እንቅስቃሴዎችን በማድረግ ላይ ትገኛለች፡፡

*ሐመር*፡- በአሁኑ ወቅት በገጠር ያሉ ካህናት ወደ ከተማ እየተሰደዱ በዚያ ያሉ አድባራትና ገዳማት እየተዘጉ ይገኛል፡፡ በእርስዎ አስተያየት ይህ ከምን የመጣ ነው ይላሉ? ይህን ጉዳይ ለማስተካከልስ ቤተ ክርስቲያን እየወሰደች ያለችው ርምጃ ምንድን ነው?

*ቅዱስነታቸው*፡- ልጆቼ የቤት ችግር አይደበቅምና እናንተም በግልጽ ስለጠየቃችሁኝ እኔም በግልጽ መመለስ ይጠበቅብኛል፡፡ ከምእመናን ኢኮኖሚያዊ አቅም ማነስ የተነሣ መረዳት ሳይችሉ ሲቀሩ ይሰደዳሉ፡፡ ይህ የሆነበት የመጀመሪያው ምክንያት የምእመናን ኢኮኖሚ ማነስ ነው፡፡ ካህናት እያገለገሉ የሚገለገሉት በምእመናን በመሆኑ ምእመናኑ አገልጋዮቻቸውን መርዳት አልችል ሲሉ ካህናቱ ወደሚያገኙበት ከተማ ይሰደዳሉ፡፡ ሌላው ምክንያት ቤተ ክርስቲያን ለረጅም ዘመናት የነበራት ሀብትና ንብረት በሙሉ መወረሱ ነው፡፡ በዚህ የተነሣም አገልጋዮቿን በሚገባ ልታስተዳድር አልቻለችም፡፡ ይህ ደግሞ ይኸውና ካህናቱ የገጠሩን እየተዉ ወደ ከተማና ሊገኝ ወደሚችልበት እንዲጎርፉ አድርጓቸዋል፡፡ በገጠር ያገለግሉ የነበሩ ካህናት ቀድሞውንም አንድ ሁለት ተብሎ ተቆጥሮ የሚሰጣቸው ደመወዝ አልነበራቸውም፡፡ ደመወዛቸው በቤተ ክርስቲያኗ ባለቤትነት ከተቀመጠላቸው መሬት የሚያገኙት እህል ነበር፡፡ ያ ዛሬ እንዳይሆን የቤተ ክርስቲያን ርስተ ጉልት በሙሉ ተወርሷል፡፡ ካህናት ሰዎች ናቸውና ይርባቸዋል፣ ይጠማቸዋል፡፡ በመሆኑም ወደ ሚያገኙበት ቦታ እየተዘዋወሩ ያገለግላሉ፡፡

አሁን ቤተ ክርስቲያን ምን ርምጃ እየወሰደች ነው? ለተባለው በገጠርም ሆነ እዚሁ በከተማዎች በተለይ በአዲስ አበባ ባሉ ብዙ ምእመናን ስላሉ በዚያ የተነሣም አድባራቱ የገቢ ምንጫቸው ደህና ስለሆነ የተዘጉ አድባራት መርጃ በሚል ምጽዋቶችን፣ አልባሳትንና ለዩ ልዩ ንዋያተ ቅድሳትን የሚያሰባስብ ኮሚቴ ስለተቋቋመ ይህ ኮሚቴ እስካሁን ያገኘውን በመርዳት ላይ ይገኛል፡፡ በወንጌሉ ትምህርት መሠረትም እዚህ ያሉ ባለጸጋ አድባራት ንዋያተ ቅድሳትና ገንዘቦችን ላጡት ሊሰጡ ተስማምተው የገጠር አድባራት እየተረዱ ነው ያለው፡፡ አገልጋዮችም ቢሆኑ ሁሉንም እስካሟላንላቸው ድረስ በየገጠሩ ሄደው ለማገልገል ፈቃደኝነታቸውን ገልጸውልናል፤ እያገለገሉም ነው፡፡ በዚህም መሠረት መንሳዊነትን በማስቀደም በቋሚነትም ባይሆን ለተወሰኑ ዓመታት ወደ ገጠር ሄደው እንደሚያገለግሉ ቃል ገብተውልናል፡፡ ያ ጉዳይ ደግሞ ቋሚ የሚሆንበትን መፍትሔ ለመሻት ከላይ ያልኩትን በማድረግ ላይ ነን፡፡

*ሐመር*፡- ብዙ አፍሪካውያን የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታስተምራቸው ዘንድ ይጠብቋታል፡፡ እንዲያውም አንዳንድ የጥቁር ሀገሮች የጸሎት ቤቶችን በመክፈት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን እያሉ ሰይመዋል፡፡ ነገር ግን የቤተ ክርስቲያኗን ሥርዓት አልተማሩም፡፡ በዚህ ረገድ ቤተ ክርስቲያን እነዚህን ወገኖች ለማስተማር ምን ያህል ዝግጁ ናት?

*ቅዱስነታቸው*፡- እኔ ጥያቄውን መቶ በመቶ ማስተናገድ ይገባናል ብዬ አምናለሁ፡፡ ምናልባት አላሟላነው ከሆነ ምክንያቱ ምንድነው ልንል ይገባል እንጂ ጥያቄው ተገቢ ነው ባይ ነኝ፡፡ የምልበትም ጥሩ ምክንያት አለኝ፡፡

በዓለም ላይ ያሉ ጥቁሮች አምላክ የላችሁም፣ ታሪክ የላችሁም ተብለው ለብዙ መቶ ዓመታት ይሰቃዩ ነበር፡፡ ጌታችንና መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ሊያመልኩ የምድር ገዢዎቻቸውና በባርነት ይገዙዋቸው የነበሩ ሰዎች እኛ ጌቶቻችሁ ሳንፈቅድላችሁ ስሙን እንኳ መጥራት አይገባችሁም ሲሏቸው የኖሩ ናቸው፡፡ በዓለም ላይ ካሉት ጥቁሮችና የጥቁር ሀገሮች እንዲህ ዓይነቱ ታሪክ ያላጋጠማቸው ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን ናቸው፡፡ በነፃነቷ ለ3000 ዘመናት ያህል ክብሯ ያልተነካ ሀገር ይህቺ ሀገር ብቻ ናት፡፡ በዓለም ላይ ያሉ የታሪክ ጸሓፊዎች አገሌ የሚባል ሰው የኦሪትና የሐዲስ ሥርዓት የወሰደላቸው ተብሎ የማይነገርላቸው ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን ናቸው፡፡ ኢትዮጵያ እንደ ሌሎች ሀገሮች በሰው ስም የተሰየሙ ሃይማኖት የሌላት ሀገር ናት፡፡ ኢትዮጵያ የኦሪትም ሆነ የሐዲስ መምህሯ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ብቻ ነው፡፡ ይህንንም የምንለው ደግሞ በመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃነት ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ የኢትዮጵያን የ3ሺ ዘመናት ታሪክ ይናገራል፡፡ ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚብሔር የሚለውን ይህንን ያስገነዝባል፡፡

ኢትዮጵያ ያላት ረዥም ታሪክ ከሰው የተቀበለችው አይደለም፡፡ ከእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ የተቀበለችው ነው፡፡ ጥበቡን የገለጠላትም ታላቁን ሐዋርያ ወደ ኢትዮጵያዊው አባታችን የወሰደው እግዚብሔር መንፈስ ቅዱስ ነውና፡፡ ስለዚህ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ክርስትናን በኢትዮጵያዊው ጃንደረባ አማካኝነት በዓለም ላይ ላሉ ጥቁሮች ነው የሰጠው፡፡ ጌታችንና መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዕፀ መስቀል ላይ ተሰቅሎ ሳለ ለሚወደው ሐዋርያ ዮሐንስ “እነኋት እናትህ” ብሎ በሰጠው ጊዜ በዮሐንስ አንጻር እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ለአማንያን ሁሉ እንደተሰጠች ነው የምናምነው፡፡ እነሆ ልጅሽ ሲልም እንደዚሁ፡፡

ስለዚህ እንደዚሁ በኢትዮጵያዊው አባታችን የተሰጠው ትምህርት ለኢትዮጵያውያን ከፍ ሲልም ለጥቁሮች ሁሉ ነው፡፡ በእውነቱ በመጽሐፍ ቅዱስ ያሉ ቃላት ስለ ኢትዮጵያ ምን እንደሚሉ ልጆቼ እንዲከታተሉ አሳስባለሁ፡፡ ታሪካቸው የጠራ በመሆኑ ጥቁር ቆዳ ያለው ሁሉ የሚኮራበት ነውና፡፡ አፍሪካውያኑም ቢሆኑ እንዲህ ብለው በመናገራቸው መገረም የለብንም፡፡ እንዲያውም ሰንፈዋል፡፡ በመጀመሪያ ጊዜ ያወቁትን እንዳያሳውቁ ያላወቁትን እንዳይጠይቁ ተጽዕኖ ነበረባቸው፡፡ ይህ በመሆኑ ብዙ ጊዜያት አልፈዋል፡፡ ዛሬ ግን ዓለም ድሮ ይሠራው የነበረውን ግፍ የዓለም ጥቁር ሕዝብ እንዲያይ ዓይኑ በተገለጠ ጊዜ፣ እርስ በርሱም በተገናኘ ጊዜ የሚያጋልጣቸው ስለሆነ በመጠኑም ቢሆን እንዲማር ታሪካን እንዲያጠና ነፃነት ሰጥቶውታል፡፡ ይሁን እንጂ ከተማሩትና ከአጠኑትም የተወሰኑት በብዛት ማለት ይቻላል በዚያው ተገድደው በተቀበሉት ይኖራሉ፡፡

እንግዲህ ቤተ ክርስቲያናችን እንደ ታሪክ ማኅደርነቷ ምን እያደረገች ነው? ለተባለው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ባለፉት ጊዜያት ያንን እንድታደርግ ሁኔታዎች አይፈቅዱም ነበር፡፡ አሁን ግን ተመቻችቷል፡፡ አቅሙ ግን የለም፡፡ አሁን እኮ ቤተ ክርስቲያናችን ባዶ ናት፡፡ ገንዘብ የላትም፡፡ ወንድሞቻችን አፍሪካውያንን ለማስተማር መሠረታዊ እንዲሁም ሰፊ ሥልጠናና ትምህርት ያስፈልጋል፡፡ ሊቃውንትን እያሰለጠን እንደኛው ጥቁር ቆዳ ላለው ማስተዋወቅ፣ ወደ እኛና ይህ ታሪክ የአንተም ነው እያልን ማቅረብ ማስተማር አለብን፡፡ ያንን ለማድረግ ደግሞ ገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ ነገር ግን ያ የሚያስፈልገው ገንዘብ የለም፡፡

የሆነው ሆኖ ቤተ ክርስቲያን ባላት ውሱን አቅም መንቀሳቀሷን አላቆመችም፡፡ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ የወጠኑትን ውጥን በመቀጠል የውጭ ግንኙነታችንን በተለይ ከጥቁሩ የአፍሪካ ሕዝብ ጋር ቀጥለናል፡፡

ጽ/ቤቱ ናይሮቢ የሆነውና ኢትዮጵያ በመሥራች አባልነት የተሳተፈችበት የመላ አፍሪካ አብያተ ክርስቲያናት ኅብረት 7ኛ ጉባኤውን በኢትዮጵያ እንዲያደርግ ጋብዘን በ1969 ዓ.ም. በጥቅምት ወር ጉባኤው በአዲስ አበባ ተደርጓል፡፡ በዚያ ጉባኤ ባለን ውስን አቅም የቻልነውን ሁሉ አድርገናል፡፡ በአዲስ አበባ ያሉትን ጥንታውያን አድባራትና ገዳማት በየበዓላቶቻቸው ተገኝተው ሥረወጥ የሆነውንና በምዕራባውያኑ ኦርጋን ያልተቀነባበረውን የቅዳሴና የማኅሌት ሥርዓት በጥቅሉ አፍሪካዊ የሆነውን ሃይማኖት፣ ሕንፃ ቤተ ክርስቲያን፣ የአምልኮት ሥርዓት እንዲያዩ አድርገናል፡፡ በጣም የሚገርመው በወቅቱ ጎብኚዎቹ የጠየቁት ጥያቄ ነበር፡፡ ሁሉም በመገረም የሚጠይቁት "በእርግጥ ይህ ሁሉ የጥቁር ነው? ነጭ አያዝበትም" የሚል ጥያቄ ነበር፡፡

በዚህ ጉባኤ በእውነቱ እኔ ንግግሬን በግልጽ ነበር ያደረኩት፡፡ ለምንድን ነው መጥታችሁ ታሪካችሁን የማታውቁ የማታጠኑት" ለምን ስለ ታሪካችን ስለ እምነታችን ሥርዓት አንነጋገርም በእርግጥ ታሪካችንን እንዳናጠናና እንዳንመረምር የሚያደርገን የነበረው የቅኝ ግዛት ቀንበር ከአህጉራችን ሙሉ በሙሉ ወጥቷል? አሁን በተገኘው ነፃነት ተጠቅመው ወደ ሃይማኖታቸው፣ ወደ ታሪካቸው በመመለስ ፋንታ እስካሁን በባርነት ያሉ የሉም ወይ? ብዬ ተናግሬ ነበር፡፡

እና ልጆቹ የአቅም ጉዳይ ሆነና እንጂ ብዙ መሥራት ይገባን ነበር፡፡ ከዚያው ከእነሱ ልጆችን በማምጣት በማሠልጠን እዚህ እንዲያድጉ በማድረግ ተምረው እንዲያስተምሩ ማድረግ ከቤተ ክርስቲያናችን የሚጠበቅ ነው፡፡ ይህንኑ እየሞከርነው ቢሆንም በጣም በከበደ ሁኔታ ነው፡፡ ከዚያ አንጻር ነው እንጂ ጥያቄው ተገቢና በአስቸኳይ መመለስ ያለበት ጥያቄ ነው፡፡ ነገር ግን አቅም ያስፈልገናል፡፡

*ሐመር፡-* በአሁኑ ወቅት በብዙ ቦታዎች የቀብር ቦታ ጥበት ይታያል፡፡ ይህንንም ችግር ለማቃለል በየክልሉ አስተዳደር በኩል የቀብር ቦታን ለመስተዳድር የቀረበ ዐሳብ አለ፡፡ ከዚህ አንጻር ይህን የቦታ ችግር ለማቃለል በቤተ ክርስቲያን ምን ታስቧል?

*ቅዱስነታቸው፡-* ይኸኛው ጥያቄም እጅግ ወቅታዊ ነው፡፡ በእውነቱ በዚህ የተነሣ በልዩ ልዩ ቦታዎች በተደጋጋሚ ችግሮች ሲከሰቱ ይታያል፡፡ እስካሁን ድረስ ቤተ ክርስቲያናችንን ያሳወቃት ሥርዓቷን ጠብቃ መቆየቷ ነው፡፡ እኛ ምናልባት እንዲህ ቢሆን የሚል ሥርዓት የለንም፡፡ ቤተ ክርስቲያን ልጆቿ ሀብቶቿ በመሆናቸው ገና በማኅጸን ሲጸነሱ ጀምራ በሰላም እንዲመጡ በጸሎቷ እያሰበች ከመጡ በኋላም በ40ና 80 ቀናቸው ሀብተ ወልድና ስመ ክርስትና ትሰጣ ቸዋለች፡፡ ለአቅመ አዳምና ሔዋን ሲደርሱ ድራ ኩላ ለወግ ለማዕረግ ታበቃለች፡፡ ከዚያም እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በሰበካ ጉባኤ ስታገለግል ቆይታ ሲያርፉ አስከሬናቸውን በቅጽሯ እንዲያርፍ አድርጋ ለነፍሳቸው ድኅነት ትጸልያለች፡፡ ይሁንና እንደተባለው በአሁኑ ወቅት የቀብር ቦታ ጥበት ችግር ተከስቷል፡፡ ይህም የሆነው በቤተ ክርስቲያን የአገልግሎት ዐውድ መስፋት የተነሣ ነው፡፡ ድሮ የቤተ ክርስቲያን ጓሮ ሁሉ ለዚህ አገልግሎት ነበረ የሚውለው፡፡ አሁን ግን እንዳልኩት ቤተ ክርስቲያን ልጆቿን በሠርክ ጉባኤ በሰንበት ትምህርት ቤቶች ወዘተ እያገለገለች በመሆኑ ችግሩ ሊከሰት ችሏል፡፡ የሆነው ሆኖ ችግሩ ከተለያዩ አድባራት ከመቅረቡ ባሻገር እራሳችንም በመገንዘባችን በተለይ የአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት ችግሩ የጎላበት በመሆኑ በከተማው ዳርቻዎች ላይ ቦታ እንዲሰጠን ጠይቀን መልሱን በመጠበቅ ላይ ነን፡፡ እነዚህ ቦታዎች ከተሰጡን ጸሎተ ፍትሐት የሚደረስባቸው አንድዳንድ ቤተ ክርስቲያን ሠርተን በሞት የተለዩን ወገኖቻችንን በዚያ እንዲያርፉ እናደርጋለን፡፡

*ሐመር፡-* በመጻሕፍት በኩል በተለይ ምእመናን በቀላሉ ሊያገኟቸው የማይችሏቸውን መጻሕፍትን ትርጉም በሚመለከት ጥሩ ጅምር አንዳለ ይታያል፡፡ ነገር ግን አዳዲስ ድርሰቶች ለሕትመት ይበቁ ዘንድ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንቷን ምን ያህል እያበረታታች ነው?

*ቅዱስነታቸው*፡- መቼም ልጆቼ እኛ ኢትዮጵያውያን ያሉን መጻሕፍቶቻችን በሚገባ ተዘጋጅተው በትውልዱ እጅ ቢገቡ በእውነቱ ከውጭ ምንም አንፈልግም ነበረ፡፡ ስለዚህ እንደተባለው እነዚህ መጻሕፍቶቻችን ትውልዱ እንዲረዳቸው አድርጎ በማዘጋጀት ማቅረብ እንደሚገባ በማመናችን በመጠነኛ እንቅስቃሴ ላይ እንገኛለን፡፡ ታዲያ ይህንን ስናደርግ አዳዲስ መጻሕፍት መደረስ እንዳለባቸውና ለዚያም መንቀሳቀስ እንዳለብን አልረሳንም፡፡ እውነት ነው ሊቃውንት ዕውቀታቸውን በመጻሕፍት መልክ ለልጆቻቸው ማስተላለፍ አለባቸው፡፡ ነገር ግን ከአሳሳቢነቱ አንፃር ለአሁኑ ትኩረት የሰጠነው ለጥንታውያኑ የብራና መጻሕፍት ነው፡፡ እነዚህ መጻሕፍት እየጠፉ እየተረሱ ነውና፡፡ የተባለውን አዳዲስ መጻሕፍት የመድረሱንና የማበረታታቱን ሥራ የሚሠሩ ሰዎችም እንዲሠማሩ ተደርጓል፡፡

*ሐመር*፡- ስለ መጻሕፍት ዝግጅት ስናነሣ በዓለም ሊቃውንት ዘንድ "የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ" /Ethiopic Bible/ በመባል የሚታወቀውና ከአበው ተያይዞ ሳይበረዝ ሳይከለስ በግዕዝ ቋንቋ ተጽፎ የሚገኘው መጽሐፍ ቅዱስ እየተተረጎመ እንደሆነ ሰምተናል፡፡ ለመሆኑ የመጽሐፉ ዝግጅት ምን ደረጃ ላይ ደርሷል?

*ቅዱስነታቸው*፡- እውነት ነው ዝግጅቱ ተጠናቆ ወደ ማተሚያ ቤት በመሄድ ላይ ነው፡፡ ይህ መጽሐፍ ቅዱስ እስከ አሁን ከነበሩት የተለያዩ ትርጉሞች የተለየና በራሷ ሊቃውንት በጥንቃቄ የተተረጎመ ነው፡፡

*ሐመር*፡- በግልዎስ መጽሐፍ ጽፈው ለንባብ አላበቁም፣ ወደፊትስ አያስቡም?

*ቅዱስነታቸው*፡- በትምህርት ዓለም ሳለሁ የታላቁን ሊቅና የመንፈስ ቅዱስ አባቴን የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስን የሕይወት ታሪክ በእንግሊዝኛና በአማርኛ ቋንቋ አዘጋጅቼ አሳትሜአለሁ፡፡ አሁንም ቢሆን ጊዜ ያጥረኛል እንጂ አዘጋጅቶ ለማሳተም ፍላጎቱ አለኝ፡፡ በእውነቱ መጻሕፍት ታትመው ሲወጡ እጅግ እቀናለሁ፡፡ ታዲያ ብቀና መቼ ሆነ? መጻሕፍትኮ የነጻነት ጓደኞች ናቸው፡፡ እንግዲህ እግዚአብሔር ቢፈቅድልኝ ወደፊት አዘጋጅ ይሆናል፡፡ ለአሁኑ ግን የቀን ከቀን ውሎዬን /Diary/ ከመሥራት ውጭ መጻሕፍትን የማዘጋጅበት ጊዜ የለኝም፡፡

*ሐመር*፡- በቤተ ክርስቲያናችን ታሪክ 19 40ዎቹና 50ዎቹ ወጣቱ የመናፍቃንን ወረራ ለመመከት በቤተ ክርስቲያኗ አጸድ መሰባሰብ የጀመረበት ወቅት ነው፡፡ ያንን እንቅስቃሴ ማእከላዊ ለማድረግ ቤተ ክርስቲያን ባደረገችው እንቅስቃሴ ደግሞ እርስዎ ወሳኝ ሚና እንደተጫወቱ እንዲያውም ቤተ ክርስቲያን ያቋቋመችው ማእከላዊ ቢሮ ሊቀመንበር እንደነበሩ ይታወቃል፡፡ የማኅበሩ /የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን የወጣቶች ማኅበር/ ሊቀ መንበር ነበሩ፡፡ ለመሆኑ በወቅቱ የነበረውን የወጣቱን እንቅስቃሴ እንዴት ያስታውሱታል?

*ቅዱስነታቸው*፡- በዚህ ጉዳይ በእውነቱ ልጆቼ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ እንጂ እኔ ልመሰገን አይገባም፡፡ ቅዱስነታቸው የወጣቱን በቤተ ክርስቲያን አካባቢ መሰባሰብ ጠቃሚ መሆኑን ተገንዝበው እንቅስቃሴውን ሁሉ ይደግፉ ነበር፡፡ በመሆኑም አሁን እናንተ በወር በወር እዚህ በስብከተ ወንጌል አደራሽ እንደምትሰበሰቡ ሁሉ ያኔም በቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ በነበሩ ወጣቶች አሰባሳቢነት በሳምንት በሳምንት እየተሰባሰቡ መማማር ጀመሩ፡፡ በመሆኑም ወጣቱ ቤተ ክርስቲያኑን እያወቀ ሊያገለግላትም ቃል እየገባ በመሄዱ ቤተ ክርስቲያን የኢትዮጵያ ትምህርት ሚኒስቴር ሆና ነበር፡፡ ታዲያ በወቅቱ እኔም በቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ እማር ስለነበር ንቁ ተሳታፊ ነበርኩ፡፡ ከዚያ እግዚአብሔር ፈቅዶ ለትምህርት ወደ ውጭ ሄጄ ቆይቼ ስመለስ ከቀድሞው የበለጠ ወጣቱ ተጠናክሮ በየቀኑ በሬዲዮ ሳይቀር የወንጌል ትምህርት እየተሰጠ ቤተ ክርስቲያን የወጣት ማኅበራቱን በያሉበት እየተንከባከበች፣ በሁኔታው እየተሳቡ ቀድሞ ያልቀረቡ ወጣቶች በየማኅበራቱ

እየታቀፉ አገኘኋቸው፡፡ ጉዳዩ በጣም እየሰፋ ቢመጣም ቤተ ክርስቲያን በሥሯ አድርጋ ለማንቀሳቀስ ስለፈለገች በዚህ በመንበረ ፓትርያርክ "የወጣቶች ማእከላዊ ጽ/ቤት ይቋቋም ተባለና እንቅስቃሴው ተጀመረ፡፡ በመኪና እየዞርን በማስተማር ወጣቱን በቤተ ክረስቲያን ለማደራጀት ቅስቀሳ ጀመርን፡፡ ደግሞ በሰንበት ት/ቤት ወጣቶች ተመዝግበው በልደት፣ በትንሣኤና በሌሎች ዓበይት በዐላት ዝግጅቶቻቸውን ለሕዝብ በማቅረብ ወጣቱን የበለጠ መሳብ ተጀመረ፡፡ አስታውሳለሁ ዝግጅቶቻችንን ወደ ብሔራዊ ቴአትር ወስደን ለሕዝብ አቅርበን ነበር፡፡ በዚያ ጊዜ ብሔራዊ ቴአትር በዚያው ያስቀራቸው ነበር፡፡ እንዲያውም አሁን በቅርብ ጊዜ በአንድ ቤተ ክርስቲያን አገልግዬ ስመጣ አንዲት ሴት መጥታ በዚያ ዓመተ ምሕረት ወደ ብሔራዊ ቴአትር ሄደን በዚያው ተቀጥረን ከቀረነው አንዷ ነኝ አለችኝ፡፡

በዚያ ወቅት ከእኛ ጋር መገናኘት የሚፈልጉ አንዳንድ የውጭ ሀገራት ለቤተ ክርስቲያናችን ወጣቶች ለአንድ ዓመት "የውጭ አገር የቤተሰብ ጉብኝት" የሚል ፕሮግራም ነበር ታዲያ ዕድሉን በሌላ መልኩ ብንጠቀምበት ተጠቃሚዎች እንሆናለን በሚል ለቅዱስነታቸው አሳሰብኩ፡፡ ይኸው በየሰንበት ት/ቤቱ በሚቀርቡ ዝግጅቶች ላይ ብልጫ ያላቸው ተማሪዎች ወደ ውጭ ሄደው ትምህርት ቀስመው እንዲመጡ ሆኖ ቤተ ክርስቲያናቸውን ከፍ ሲልም አገራቸውን እንዲጠቅሙ ይሁን የሚል ነበር፡፡ በዚያም መሠረት በርካታ ወጣቶች ወደ ውጭ ሀገር እየሄዱ ይማሩ ነበር፡፡

*ሐመር*፡- ያኔ የነበረውን የወጣቱን እንቅስቃሴ ከዛሬው ጋር ሲያመዛዝኑት የሚያዩት ዕድገትን ነው? ወይስ ድክመትን?

*ቅዱስነታቸው*፡- አይ ዕድገትን ነው የምመለከተው፡፡ በእውነቱ ያና ይኸኛው ጊዜ ተገናኝተው ቢሆን ኖሮ እንዴት ጥሩ ሥራ ይሠራ ነበር? ምን ይሆናል አልተገናኙም፡፡ በዚያን ጊዜ ቤተ ክርስቲያን ብዙ ሀብትና ንብረት ነበራት፡፡ አሁን ግን ወጣቱ ከጥበባዊ አመለካከት ጋር በቤተ ክርስቲያን ተሰባስቧል፡፡ ገንዘብ ደግሞ የለም፡፡ ታዲያ ያኔ የነበረው ገንዘብና አሁን ያለው የወጣቶች ገንቢ አመለካከትና ቤተ ክርስቲያን ሥር መሰባሰብ ቢገናኙ ኖሮ ጥሩ ሥራ መሥራት እንችል ነበር፡፡ የአሁኑ ወጣት ደጋፊ ሳይኖረው በራሱ ጥረት በራሱ ፍላጎት ተሰባስቧል፡፡ እንዴ እናንተ ምን አድርጋችሁ ነው በወር በወር በዚህ ግቢ ሰፊው አዳራሽ ጠቦ ግቢው በሰዎች እስከሚመላ ድረስ የምትሰበሰቧቸው፡፡ በእውነቱ በአሁኑ ወቅት ንቃት ያለው ወጣት በቤተ ክርስቲያን ተሰባስቧል፡፡ ታዲያ ይህንን ንቃቱን ይዞ የሚንቀሳቀስበት ቢያገኝ ኖሮ ተአምር ይሠራ ነበር፡፡ በወቅቱ ብዙ ችግር ነበር፡፡ አሁን ግን እኛ አባቶች የእናንተን መሰባሰብና ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ቀድማችሁ መገኘታችሁን ስናይ እጅግ ደስ ይለናል፡፡ ነገር ግን ይህን እንቅስቃሴያችሁን የምታፋጥኑበት ገንዘብ እንደሚያስፈልጋችሁ ብናምንም ገንዘብ ስላጣን እናዝናለን፡፡ የሆነው ሆኖ ጅምራችሁ ጥሩ ነውና ወጣት የቤተ ክርስቲያን ልጆች ሁሉ በርቱ እላለሁ፡፡

*ሐመር*፡- በአሁኑ ወቅት ወጣቱ የቤተ ክርስቲያኑን ትምህርት እንዲያገኝ ከሰንበት ትምህርት ቤት መርሐ ግብራት ሌላ የተዘጋጀለት ነገር አለ?

*ቅዱስነታቸው፡-* በዚህ በሀገር ውስጥ ለተባለው ያቀድነው ዕቅድ ባሉን ሁለት መንፈሳውያን ተቋማት ማለት በቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅና በሰዋሰወ ብርሃን ከፍተኛ ወንፈሳዊ ትምህርት ቤት የማታ ትምህርት ለማስተማር ነው፡፡ ለዚህም ጥናቱ አልቋል፡፡ የቀረው ሥራውን መጀመር ነው፡፡ ከሚመለከታቸው ክፍሎች ጋር ተነጋግሮ መተማመን ይቀረኛል፡፡ ከዚህ በፊትም ከወጣቶቹ ጥያቄ ቀርቦልኛል፡፡ እኔም ጥያቄያቸውን ተቀብዬዋለሁ፡፡ ምክንያቱም ጥራት ያለው ትምህርት ከተሰጠ ወጣቶች ብቻ ሳይሆኑ ምእመናኑም ተጠቃሚዎች ይሆናሉና፡፡

*ሐመር*፡- ለቅዱስነትዎ ረጅም ዕድሜ ይስጥልን፤ ቡራኬዎ ይድረሰን፡፡

*አዘጋጁ*፡- ከቅዱስ አባታችን ጋር ይህንን ቃለ መጠይቅ ያደረግነው ሰበታ ቤተ ደናግል ገዳም ቀኑን ሙሉ ውለው ደክሟቸው በመጡበት ሰዓት ነው፡፡ ድካምን አሸንፈው እስከ ምሽቱ አምስት ሰዓት ከእኛ ከልጆቻቸው ጋር በማምሸታቸው በአንባብያን ስም ከፍ ያለ ምሥጋናችንን እናቀርባለን፡፡

***ምንጭ፡- ሐመር 7ኛ ዓመት ቁጥር 2 ሚያዝያ/ግንቦት 1991 ዓ.ም.***